የኢሕአዴግ ሚሊየነርስ

አበበ ኩሊው፣ነጋሽ ደሃ ገበሬውና እትዬ መሰረት የጉልቷ ነጋዴ

ልማታዊው መንግስት ኢሕአዴግ ከራሱ አባላትና ደጋፊዎች አልፎ ሌላውንም ደሃ ሚሊየነርስ አድርጌአለሁ እያለ ማውራቱና በአደባባይ ሰዎችን ማቅረቡ የተለመደ ነው።ታዲያ በራሱ ዙሪያ በአንድ ጀንበር የተፈጠሩት አዲስ ሚሊየነሮች ታሪክ እውነት ቢሆንም በደሃው ኢትዮጵያዊው ጎራ ተፈጠሩ የተባሉት ሚሊየነርስ እንዴትና እነማን እንደሆኑ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ቢያውቃቸው የደስታቸው ተካፋይ እንጂ የሚከፋው ይኖራል ብዬ አልገምትም።ቀና አይምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ደሃው ወገኑ እንዲያልፍለት፣የተሻለ ኑሮ እንዲኖር ይፈልጋል እንጂ በድህነት ተወልዶ በድህነት አድጎ በድህነት ተቆራምቶ የደሃ ሞት እንዲሞት አይሻም።በትግል ሜዳም የተሰለፈውና መስዋእትነት የሚከፍለው አብዛኛው ለዚያ ግብ ነው።

ወደ ድሆቹ "ሚሊየነርስ" ታሪክ ልመለስና

አበበ ኩሊው እድሜ ልኩን በሰፈር ወፍጮቤት የሚፈጭ ዱቄት፣ከታክሲ ለሚወርድ ሻንጣ፣ከጉልት ለሚገዛ ሸቀጥ ተሸክሞ የሚያደርስ ሰፈርተኛው የሚያውቀውና የሚወደው ኩሊ ነው። አቤ የደንበኞቹን ስምና ማን የት እንደሚኖርም ያውቃል፤አብዛኛዎቹ አቤን አድርስልኝ ብለው ወደሌላ ትካራቸው ይሄዳሉ እንጂ ከኋላ ተከትለው በዚህ ግባ በዚህ ውጣ አይሉትም ወይም ተጠራጥረው በአይነቁራኛ አይከታተሉትም።ታዲያ አንድ ሰሞን አቤ ከሰፈሩ ይሰወራል፣ጓደኞቹና ደንበኞቹ አቤ የት ገባ?ምን ዋጠው?አደጋ ደርሶበት ወይስ ታሞ ተኛ ብለው መጨነቅ ጀመሩ።አቤ ሰላማዊና ተግባቢ በመሆኑ ክፉ ነገር ሰርቶ ወይም ተጣልቶ ታሰረ ብሎ የጠረጠረው የለም። እርግጥም አልታሰረም፣ታሞም እቤት አልዋለም።አንድ የተለዩ አጋጣሚ ገጥሞት ነበር የተሰወረው።

አንድ ማታ ላይ ሰፈረተኛውና ጓደኞቹ ባልጠበቁት ሰዓት አቤ ሽክ ብሎ ብቅ አለ።የታየው በአካል ሳይሆን በቴሌቪዥን ነው። አቤ ኩሊው፣አዲሱ የተሳካለት ነጋዴ ተብሎ ለዚህ ያበቃውን መንግስት እያደነቀ ከድህነት መገላገሉን አበሰረ።የሚያውቀው ሁሉ በመገረምም በመደንገጥም እሱ መሆኑን ተጠራጠረ፣እርስ በርሱም አቤ ነው አይደለም እያለ መጠያየቅ ጀመረ።አቤ ግን አዲስ ልብስ ከመልበሱ በስተቀር ያው አቤ ነው፣አልተለወጠም፤ደልቶት አልወዛም፣አልወፈረም።አቅራቢው ጋዜጠኛ

እያሞገሰና እየካበው በትያትሩ አቤም ተገርሞ መሽኮርመምና ፈገግ ማለት ጀመረ።በዚህ ጊዜ ነበር አቤ መሆኑ የተረጋገጠው። አገር የሚያውቃት አንዷ ሽራፋ የፊት ጥርሱ እንኳን አልተቀየረችም እዛው እቦታዋ ላይ ሆና ፈገግ ሲል አጋለጠችው።

ከዚያ ቲያትር በኋላ ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ ተባለና አቤም ወደ ዱሮ ሰፈሩ ተመለሰ፣፤ግን ሲመለስ ዱሮ የሚያውቀው ሰፈረተኛና የሙያ ጓደኛ በናፍቆትና በፍቅር አልተቀበለውም።ሁሉም በእልህ ምን ልታደርግ መጣህ? ሚሊየነር ሆነህ የለም እንዴ?ነው ወይስ ልታካፍለንና ከድህነት ልታወጣን? እያለ በጥያቄ ያዋክበው ጀመር።አንዳንዱም አሻጥሩ ገብቶት የተበሳጨው ሂድ ጥፋ፤አቃጣሪ! እያለ አፈጠጠበት።አቤ ግን እምባው ቁርዝዝ ብሎ፣ የሚወደው ሰፈርተኛና የሸክም ጓደኞቹ ፊት ሲነሱት የተፈጠረውን ሁኔታ በእርጋታ  እንዲህ ሲል ማስረዳት ጀመረ።አንድ ቀን ማለዳ ላይ የማላውቃቸው ሰዎች ሁለት ብር በወር እየከፈልኩ በደባልነት ከተኛሁበት የቀበሌ ጎጆ መጥተው ትፈለጋለህ ብለው ወሰዱኝ።ቁርሴን አብልተው መንግስት በዝዋይ ውስጥ የሚሰራው የስብሰባ አዳራሽ ስላለ ብዙ ሰራተኛ ስለሚያስፈልግ ወደዚያ ለስራ ትፈለጋለህ አሉኝ።ግር ቢለኝም ሳላቅማማ በደስታ እሺ አልኩኝ። ዝዋይ አስራአምስት ቀን ሲሚንቶ ሳቦካ ቆይቼ ለአንድ ስራ አዲስ አበባ ትፈለጋለህ አሉኝና መልሰው አመጡኝ።ስመለስ ምሳየን አበሉኝና አንድ ልብስ ሱቅ ውስጥ ወስደው በህልሜም አይቼው የማላውቀውን ልብስ አለበሱኝ፤ከላስቲክ ሌላ አድርጌ የማላውቀውን የቆዳ ጫማም ደነቀሩልኝ።ከዛ በኋላ በካሜራ ቪዲዮ ስለምትነሳ በዚህ መንግስት እርዳታና መመሪያ ከድህነት ወጥቼ ሃብታም ለመሆን በቅቻለሁ ብለህ ተናገር አሉኝ።መንግስት ለትብብርህ ውለታህን ይከፍልሃል ተባልኩና አንድ ሁለት ጊዜ ለሙከራ የምለውን እያልኩ በቪዲዮ ተነስቼ በሶስተኛው ጊዜ ጥሩ ነው ይበቃል ተባልኩ።ያለበሱኝን አሶልቀው ወዲያው ወደ ዝዋይ መለሱኝ።ማታ ላይ ዝዋይ ገባሁ፤ የሆነውን ለማንም እንዳልናገር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ለሳምንት ያንኑ ሲሚንቶ ሳቦካ ቆይቼ ይኸው ስራ አለቀ ተባለና ተመልሸ መጣሁ።እውነቱ ይህ ነው፤እንኳንስ ሚሊየን ብር መቶ ብርም አላገኘሁም፣ ከናንተው ጋር የዱሮውን ኑሮየን ለመግፋት ተመልሻለሁ።በዚህ የነዳሁት ካለና ካጠፋሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ ብሎ እያለቀሰ ታሪኩን ደመደመ።አቤም ከዚያ ወዲህ  የወያኔ ሚሊየነር የሚል ቅጽል ስም ወጣለት።

የተሳካለት ታታሪው ገበሬ

አቶ ነጋሽ በሰሜን ሸዋ አካባቢ የሚኖር፣ የአራት ልጆች አባት፣በቁራሽ መሬት ላይ እያረሰ የሚተዳደር፣በቁና ከሚሰፈር ምርት በስተቀር ሌላ ገቢ የሌለው ሙልጭ ያለ ደሃ ሰው ነው።በዚህ የኑሮ ክበደት እያቃተተ የሚኖረው ወንድሟ ያሳዘናት አንዲ እህቱ ችግሩን ለማቃለል ስትል ሁለት ልጆቹን ለማሳደግ ወስዳ ትምህርት ቤት አሰገባች።ገበሬው ነጋሽ ከችግሩ ባይላቀቅም የሁለት ልጆቹ መትረፍ ሃሳቡን ቀነሰለት።

የከባቢው የገበሬ ማህበር አባል በመሆኑ አንድ ቀን ላይ የመንግስት ባለስልጣኖች ለስራ ትፈለጋለህ ብለው ወደ ደብረብርሃን ገበሬ ማህበር ጽ/ቤት ይወስዱታል።እንደደረሰ የኢሕአዴግ መንግስት ለገበሬው ያደረገውንና ለማድረግ የሚያስበውን በገለጻ መልክ ካስረዱት በኋላ እንደሱ ያሉትንም ድሆች ሚሊየነርስ ለማድረግ እቅድ እንዳለው ይገልጹለታል፤ አያይዘውም ይህን የመንግስት አሳብ ለሕዝብ ማስረዳት ስለሚያስፈልግ አንተ ስለተመረጥክ ሚሊየነር ሆኛለሁ ብለህ ብትናገር መንግስት የምትለውን ያደርግልሃል ተባለ።ደሃው ነጋሽ ያንን ተናግሮ ሃብታም የሚሆን መሰለውና ያሉትን ለማድረግ በደስታ ይፈነጭ ጀመር።ለትያትሩ ማዳመቂያ ድሪቶ ቁምጣ ሱሪውን ጥሎ ቦላሌ ሱሪ ታጠቀ፣በሸሚዝ ላይ ኮት ደረበበት፣ አረንጓዴ ካባ ለብሶ መዳሊያ ተሸለመና በአንገቱ ላይ አጠለቀ፣ በእግሩም ላይ ቆዳ ጫማ ደነቀረ።ሌላ ነጋሽ፣ቱጃር ነጋሽ፣ የተሳካለት ገበሬ ነጋሽ መስሎ ቁጭ አለ።ባለሞያ ጋዜጠኛ ደግኖ ባዘጋጀው የቪዲዮ ካሜራ የተሳካለት ገበሬ መሆኑን በይፋ ተናገረ።ከግማሽ ሰዓት በኋላ ትያትሩ አለቀና የለበሰውን አውልቆ ወደፊት ስትፈለግ ትመጣለህ ተባለና ባዶ እጁን ወደ ደሃ ጎጆው ተመለሰ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የተቀረጸው ቲያትር በቴሌቪዥን ታዬ፤የነጋሽ ከባቢ ቴሌቪዥን የማየቱ ዕድል የነመነመነ ነበርና ነጋሽና መሰል ገበሬዎቹ አልተከታተሉትም ነበር።በመከራ ቀን የደረሰችለት እህቱ አጋጣሚ ሆኖ እቤቷ ቁጭ ብላ ቴሌቪዥን ስታይ የወንድሟን ሚሊየነር መሆን ሰማችና ደስታና ትዝብት ተፈራረቀባት፤እሱ ነው አይደለም በሚል ብዥታ ላይ ተዋጠች፤ስምና መልኩ ግን ያው የምታውቀው የወንድሟ ነጋሽ ነው።በሁኔታው ተገርማ፣ሌሊቱ ነግቶላት ወደ ወንድሟ የምትሄድበትን ሰዓት ስታሰላስል ነጋ።በጧቱ የወንድሟን ልጆች ሰብስባ ፣እቃቸውን አሲዛ በበራሪ አውቶብስ ወደ ወንድሟ ቤት ሄደች።ስትደርስ የጠበቃት ያው ድሪቶ ቁምጣ ሱሪ የታጠቀው ደሃው ነጋሽ ነው።በመገረምና በንዴትም አቶ

ሚሊየነር! አሁን ማንን ለማደናገር ነው ድሪቶ የለበስከው፣ሚሊየነር መሆንህን ያላወቅን መሰለህ? ማን ይቀማኛል ብለህ ነው?በል ከአሁን በኋላ እንኳን የራስህን ልጆች ቀርቶ ሌሎችንም ደሃ ዘመዶችህን መርዳት ትችላለህ፣የወሰድኳቸውን ልጆችህን ተረከብ ብላ አፈጠጠችበት።ደሃው ነጋሽ መጋኛ እንደመታው ባለበት ደርቆ ቀረ፤ያላሰበው ነገር መፈጸሙ አስደነገጠው።መጮህና ማልቀስ ጀመረ።እንድትሰማው እየለመነ የሆነውን ሁኔታ ለእህቱ አስረዳት፡፤እንኳንስ ሚሊየነር ሊሞት የሚያጣጥረውን አንዱን በሬውን የሚተካበት ገንዘብ እንደሌለውና ኑሮውም በየቀኑ ከድጡ ወደማጡ እየሆነበት እንደመጣ አጫወታት።እህቱም የመንግስትን ክፋትና ውሸት ተረድታና ወንድሟም ለወደፊት እንዲህ ላለው ተንኮል መጠቀሚያ እንዳይሆንና እንዲጠነቀቅ አስረድታው ልትመልስለት የወሰደቻቸውን ልጆቹን ይዛ ወደ ቤቷ ተመለሰች።

የጉልቷ ነጋዴ ባለኮንደሚነሟ አትዬ መሰረት

በእድሜ የገፉ ቢሆንም የሰፈሩ ነዋሪ፣ትልቅ ትንሹ አትዬ መሰረት እያለ ይጠራቸዋል።አትዬ መሰረት በሰፈሩ የጉልት ገበያ በስኒ ተሰፍሮ የሚሸጥ ጥራጥሬና ፣በቆርኪ ተሰፍሮ የሚሸጥ አንዳንድ ቅመማቅመም በእራፊ አንሶላ ላይ ደርድረው የሚሸጡ አዛውንት ናቸው።ገንዘብ ያለው ከፍሎ የሌለውም ሰፈርተኛ በዱቤ ወስዶ የሚጠቀምበት ዕድል ስላለ ሁሉም ያከብራቸዋል።በተቀመጡበት የጉልት ገበያ አላፊ አግዳሚው አብዛኛው የሚያውቃቸ ስለሆነ ሰላምታ መለዋወጡ በስራ ከሚያሳልፉት ጊዜ በላይ ነው።

አትዬ መሰረት ዕድሜ ልካቸውን የሚኖሩት በኪራይ ቤት ነው፤አሁንም በቀበሌ ኪራይ ቤት ውስጥ ይኖራሉ።የቀበሌው መኖሪያ ሰፈር ለሃብታሞች በመሸጡ ካርታ ያለውም ሆነ የሌለው እየተነጠቀ እንዲለቅ በመገደዱ አንዳንዱም የኮንደሚኔም ቤት ዕጣ ተጥሎ ደርሶሃል ተባለ።ከደረሳቸው መካከል አንዷ አትዬ መሰረት ናቸው።ለኮንደሚነሙ ቤት እንዲከፍሉ የተጠየቁት የመጀመሪያ ክፍያ ሰላሳ ሽህ በር ነበር፤ያንን ለመክፈል ደፋ ቀና ሲሉ፣ከዘመድ አዝማድ እርዳታና ብድር እየጠየቁ ባሉበት ጊዜ የቤቱ ዋጋ ተቀይሮ አራት መቶ ሽህ መሆኑ ተነገራቸው።ለመከፈል ስላልቻሉ ለመክፈል የሚችለው አንዱ ዲያስፖራ ካሽ ከፍሎ ነጠቃቸው።እርይ ብለው፣መንታ እንባ እየረጩ አለቀሱ፣ዲያስፖራ ዓይንህ ይፍሰስ ብለውም እረገሙ፤ሁሉም ተቀብሎ ዲያስፖራን እረገመ። ኑዋሪው ከፍሎ መግዛትና

መጠቀም የማይችልበትን እየከፈለ ኑሮውን ያሶደደበትን ዲያስፖራ የሚባል ጨካኝና እራሱን ወዳድ፣የመንግስት የማይነጥፍ ላም፣ልጆቻችንን እያማለለ የሚያሳስት ሰይጣን ብለው አወገዙት።

አትዬ መሰረት አደባባይ ወጥተው ኢሕአዴግን ያመሰገኑበትን፣ደግፈው የጨፈሩበትን እለት እረገሙት።

የኢሕአዴግ የሚሊየን ብርና የኮንደሚነም ባለቤት ሆኑ ተብሎ የተነገረላቸው ዜጎች ኑሯቸው ሳይለወጥ  ያተረፉት ነገር ቢኖር የዕድሜ ጌትነት ብቻ ነው።በዛው ድህነት አሁንም ይኖራሉ።አቤም ከጆንያ ሸክም፣ነጋሽ.ከቁና ምርት አምራችነት አትዬ መሰረትም ከጉልት ችርቻሮ አልተላቀቁም።እነሱም ይኖራሉ፤ኢሕአዴግም እየዋሸና እየዘረፈ ይኖራል።